## የሰማዕታት ህይወት ዘለዓለማዊ ነው !

ባንዳ የበንዳ ልጅ መሠረተ ባንዳ፤

ዘር ማንዘሩ ባንዳ ሁለመናው ባንዳ፤

አባቱም አያቱም አጎቶቹም ባንዳ

ዘር ከልጓሙ ነው ለካ፤ የማይለቅ ፍዳ።

ሲገብር የኖረው የወሬ ፍሪዳ፤

ሰብዕናውን ሸጦ ለማይጠቅም ፋይዳ፤

ወገኑን አስፈጅቶ ሕዝብን እንደ ጭዳ፤

አንገቱን አላትሞ ከውርደት ግድግዳ፤

ሀገሩን ወገኑን ታሪኩን የከዳ፤

ወሬ ያቀብላል በጠላቶች ጓዳ።

እየመሰለው ነው ሀገሩን የጎዳ!

አገሪቱ እንድትሆን ሲያል ምድረ-በዳ።

ለጠላቶቿ ሲሳይ ለልጆቿ ፍዳ

ሌት ተቀን ይማስናል ላይሸፍን ቀዳዳ።

ጀግኖች ሲዋደቁ በየጦሩ ሜዳ፤

ሮጦ ያመልጣል ወደ እናቱ ጓዳ፤

ወትሮም ይባል ነበር እስከነተርቱ ፤

" ባንዳ ፈርቶ ሲሸሽ የጠቅማል ለናቱ፤

" አንዳንድ ሙጣዝ አለ ጉተና አሳማሪ፤

አንዳንድ ወሙቴ አለ ጎፈሬ አሳማሪ፤

ሲሄዱ በኋላ ሲመልሱ መሪ። "

ይባል ነበር ዱሮ በታሪክ ተነግሮ፤

ተገላልጦ ታየ አምናና ዘንድሮ !

“ ባንዳነት ለምኔ ከኅደት ለምኔ፤
ማስመሰል ለምኔ መልከስከስ ለምኔ
አልኩባይ ለምኔ ሌላ መሆን ለምኔ
እጸናለሁ እንጅ እኔ በእኔነቴ !”

ብለው የወደቁት ለሀገር መሥዋዕት፤
በቃል- ኪዳንና በዓላማቸው ጽናት፤
ለሕዝብ መመኪያ ለሀገራቸው ኩራት፤
ለታሪክ ለዕልና ለኅሌና ብቅት ፤
እንደኮሩ ሄዱ እንደተጀነኑ፤
በዓላማቸው በርታት በዕምነት እንደጠኑ፤
ከፈን አልተዋሱ መቃብሩ አልማሱ፤
ጠላት ሳይማርካቸው ከንድን ተንተራሱ ።

ሐውልት አልሰሩልት ቅኔ አልተቀኙለት፤
እንባም አልረጩለት ደረት አልመቱለት ፤
ምሾ አልወረዱለት ፤ ፍትሃት አልፈቱለት፤
ሰደቃ አልዋሉለት፤ ቁርዓን አላሰሙት ፤
የትላንቱን ረስተው ነገን አላሰቡት ፤
የጀግኖችን ታሪክ እንዲሁ አዳፈኑት ።

ለኢትዮጵያ ሠማዕታት ዘለዓልማዊ ሕይወት
ለሀገር ሻጭ የዘለዓለም ሞት !!!

ከነዓን

ግንቦት 2006 ዓም